# “ውሸትና ስንቅ እያደረ ይቀላል”!!!

ከባህልቢ ዘማርያም

## ክፍል አምስት፤

(በሐጎስ ጽሑፍ ፓራግራፍ 4 ላይ ይመልከቱ)

> *“...... የመጀመርያውና ከሞላ ጎደል በዳያስፖራው መካከል በተደጋጋሚ ጎልቶ የሚታየው ጉዳይ፤ አንድም ዳያስፖራ ከአገሩ/ከአገሯ የተሰደደው/የተሰደደችው አገራቸውንና ህዝባቸውን ለመታደግ ሳይሆን ለራሳቸው የተሻለ ሕይወት ለመኖር መሆኑ ላይ ነው።”*

እውነቱን ለመናገር ሐጎስ ዮሐንስ የሚያወሩት ስለ የተኛው ፈላሽ ወገን (ዳያስፖራ) እንደሆነ ግልጽ አይደለም (ከዚህ በኋላ “Diaspora” የሚለውን የባዕድ ቃል ለማስወገድ ሲባል በዚህ ፅሑፍ ውስጥ “ፈላሽ” በሚለው የአማርኛ ቃል ተተክቷል)። በመሠረቱ ሰዎች አገራቸውንና ህዝባቸውን ለመታደግ ወደ ሌላ አገር ይፈልሳሉ የሚለውን አባባል ይህ ፀሓፊ አይጋራውም። ለሰዎች ፍልሰት ምክንያቶች በርካቶች ናቸው። እያንዳንዱ ሰው ከአገር ለመውጣት የሚያስገድዱት የየራሱ የግል ምክንያቶች ይኖሩታል። ሆኖም እንደ ፖለቲካ፤ ረሀብ፤ ....ወዘተ የመሳሰሉ መሠረታዊ ምክንያቶች ሆነው ሲገኙ እንደ ግለሰቦች ችግር ብቻ ሳይሆን እንደማኅበራዊ ችግር ተደርገው የሚቆጠሩና መቆጠርም የሚገባቸው ናቸው። ያም ሆነ ይህ የሚፈልሰውና የሚሰደደው ወገናችን ህዝብንና አገርን ለመታደግ አልተሰደደም የሚለው አባባል ትርጉሙን የሳተ ይሆናል።

ፈላሽ ኢትዮጵያዊው ወገናችን የሚሰደድበት ምክንያት ይህ ነው ብሎ አንድ ወይም ሁለት ብቸኛ ምክንያቶችን ማቅረብ ለእንደ ሐጎስ ዓይነቱ ቀላል ሊሆን ይችል እንደሆነ እንጂ የሁኔታውን ውስብስብነት ለሚረዳ ሰው አንድና ሁለት ብሎ ምክንያቶቹን በድፍረት ማስቀመጥ ቀላል አይሆንም። የእያንዳንዱ ሰው ችግር ተለይቶ መታየት ይኖርበታል። ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ ለሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ የመፍለስ ወይም መሰደድ ምክንያት አገራቸውንና ህዝባቸውን ለመታደግ ሳይሆን ለራሳቸው የተሻለ ሕይወት ለመኖር ነው የሚለው የሐጎስ ዮሐንስ አባባል በመሠረተ ሓሳብ ደረጃ ስሕተት አይሆንም። ስሕተት የሚሆነው ጉዳዩን ከነባራዊው ተጨባጭ ሁኔታ ተነስቶ በመመርመር ፈንታ የተወሰነ የራስ ምኞትን ለማሳካት ካለው ፋይዳ አንጻር ለመተንተን መሞከሩ ላይ ነው። የሆነ ሆኖ ሰው ተሰዶም ሆነ በሌላ ዘዴ የራሱን ሕይወት ለማሻሻል ጥረት ማድረግ ባህርያዊ ነገር ስለሆነ ፈላሽ ኢትዮጵያዊያን በተሰደዱባቸው አገሮች የሚያጋጥሟቸው ችግሮችን ተቋቁመው ኑሯቸውን በማሻሻል ተሳክቶላቸው ስናይ እሰየው በማለት በደስታ ልናበረታታቸው ይገባል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን፤ በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያዊው ፈላሽ እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦን አቅልሎ ማየት ተገቢ አይሆንም። ሐጎስ ዮሐንስ ሥልጣን ለጨበጠ አምባገነን ሁሉ ያላሸረገደ ውጉዝ ከመአርዮስ ነው የሚል አቋም ካልያዙ በስተቀር ፈላሽ ኢትዮጵያዊያን በተለያየ መንገድና መልክ ወደ ኢትዮጵያ የሚልኩት የውጭ ምንዛሪ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። የ2008/2009 ዓ.ም.ፈ የዓለም ባንክ መረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ ኢትዮጵያ በተጠቀሰው ዓመት ከ3 ቢልዮን በላይ የአሜሪካን ዶላር ከፈላሽ ዜጎችዋ አግኝታለች። ይህንን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና የዓለም ባንክ የዘገቡትን ጥናታዊ ፅሑፎችንና መረጃዎችን በማገላበጥ ማመሳከር ይቻላል። ከዚህም አልፎ ባንዱም ሆነ በሌላ የተወሰኑ ከሥርዓቱ ጋር የተቆራኙ ፈላሽ ኢትዮጵያዊያን በአገሪቱ ውስጥ የተወሰነ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እያደረጉ


የትርጉም ስሕተት ቢኖርበት ይህ ፀሐፊ ሐላፊነቱን ይወስዳል።

መሆኑ ከዓይጋ ፎረም ድረ-ገጽ ጭምር ለማግኘት የሚቻል ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የተስተካከለ ሥርዓት-መንግሥት ቢኖረን ኖሮ ፈላሽ ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ከዚህ በእጥፍ ድርብ የበለጠ ማድረግ እንደሚችሉ ግን የሚያጠራጥር አይደለም። ሐጎስ ዮሐንስ ከአገሩ ፈልሶ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ በጅምላ ለመክሰስ የሚያስችል ሞራላዊም ሆነ ሕጋዊ መሠረት አይኖራቸውም።

ሌላው በስደት ስለሚኖሩት ነብሰ-ገዳዮችና የህዝብ ንብረት ዘራፊዎች ላይ የሰነዘሩት ትችት ያለ ምንም ማጣቀሻ የቀረበ ሌጣ ትችት ቢሆንም በመሠረቱ ወንጀለኞቹ ለድርጊታቸው ተጠያቂ መሆን ይኖርባቸዋል። ይህ ግን ከአገር ኮብልለው በየሥርቻው ሸሽተው ያሉትን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የመንግሥት ሥልጣን ጨብጠው በማን አለብኝነት አገርንና ህዝብን በማጥፋት ላይ የሚገኙትንም የሚያካትት መሆን ይኖርበታል። ባጠቃላይ ሲታይ ከወንጀለኛው በፊት ወንጀልን ለይቶ ማውጣት ሚዛናዊነትን እንደሚጠይቅ ሊሰመርበት ይገባል። ይህ ሲሆን በማንም ይፈጸም በማን ለተፈጸመው ወንጀል ፈጻሚው ተጠያቂ መሆን ይኖርበታል ወደሚለው ፍትሓዊ ድምዳሜ ለመድረስ ያስችለናል። እዚህ ላይ ሐጎስ ዮሐንስ የአንድን ወገን ወንጀል ሲያወግዙ በሚያደሉለት ወገን ስለሚፈጸመው ወንጀል ግን ያሉት ነገር የለም። ለምሳሌ በ1997 ዓ.ም ሀገራዊ ምርጫ ውዝግብ ምክንያት አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ የ200 ሰው ሕይወት ጠፍቷል። የጋምቤላ እልቂትም እዚህ ውስጥ የሚካተት ነው። ሩቅ ሳንሄድ በአከባቢያችን የተፈጸሙ ሊጠቀሱ የሚችሉ ብዙ ጥፋቶች የተፈጸሙ አሉ። ከዚህም አልፎ ሌሎች ብዙ ተመሳሳይ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል። ባጭሩ ባለፉት 30ና 40 ዓመታት የተፈጸሙ ወንጀሎች አንድና ሁለት ተብሎ የመቍጠር ጉዳይ አይደለም። ስለዚህ ሁሉም ጥፋቶች በገለልተኛ አካል ተጣርተው ወንጀለኞች ለፍርድ መቅረብ ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ሁሉም ወንጀለኞች ለፍርድ ይቅረቡ ብለን ብንጮህ ለፍትሕ መቆማችንን ከማመላከቱም በላይ “ፍትሕ ዕዉር ነው” የሚለው የፈረንጆች አባባልም ተግባራዊ ማድረግ ስለሆነ ሐቁን የመናገር ሞራልና ድፍረቱ ሊኖረን ይገባል። ከወንጀሉ ሁሉም የየራሱን ድርሻ መውሰድ ይኖርበታል። ከዚህ በተረፈ ይህ ፀሐፊ ለሐጎስ ዮሐንስ የሚኖረው ምክር ነገሮችን ከአፍቅሮተ-ድርጅት/መንግስት ባሻገር እንዲመለከቱ ነው። ነብሰ-ገዳዮችና አጭበርባሪዎች ከየትም ወገን ይሁኑ ከየት ለህብረተ-ሰብ ዕድገት ጠንቅ ናቸውና በሕግ ፊት ቀርበው መጠየቅ ይኖርባቸዋል።

(በፅሑፍ ፓራግራፍ 5 ይመልከቱ)

> *“በግሌ፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለመታደግ በገባው ቃል ምክንያት አካላቱን አጥቶ በመደገፍያ (crunch*= <u>crutch ለማለት ይሆናል ብዬ እገምታለሁ</u>) እርዳታ ከሚራመደው አንድ ኢትዮጵያዊ ጀግና ጋር ራሴን ሳነፃፅር ዋጋ ቢስነትና ባዶነት ይሰማኛል። በመሆኑም፣አንድ በጦርነት አካሉ የጎደለ ኢትዮጵያዊ ጀግና በዓለም ላይ አሉ በሚባሉ ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ከሚያስተምር አንድ ፕሮፌሰር የበለጠ ኢትዮጵያን ለማበልጸግ አስተዋፅዖ ያለው ምርጥ ሰትራተጂን የመገንዘብ፣ የማወቅና የመረዳት አቅም እንዳለው እርግጠኛ ነኝ።” ይላሉ። (ሰረዝ የተጨመረ)*

የሐጎስ ዮሐንስን ፅሑፍ እንደዚህ ፀሐፊ ሳይሰለች አንብቦ ለመጨረስ የቻለ ሰው፤ ፀሐፊው ያላቸው በራስ የመተማመን ውስጣዊ ስሜት ምን እንደሚመስል ለመገመት ይቸገራል የሚል ግምት ለመያዝ ይከብዳል። መጣጥፋቸው የውስጣዊ ስሜታቸውና የአእምሮ ብቃታቸው ቀጥተኛ ነፀብራቅ መሆኑም የሚያከራክር አይደለም። ስለሆነም፤ በመጣጥፋቸው ውስጥ የ“ዋጋ ቢስነትና ባዶነት ስሜት ይሰማኛል” በማለት አስፍረውት የሚገኘው ሐረግ ያለቦታው አይደለም። ይህ ፀሐፊ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በመከላከል ግዳጅ ላይ ሕይወታቸውን ላጡና አካላቸው ለጎደሉ

2 የትርጉም ስሕተት ቢኖርበት ይህ ፀሐፊ ሐላፊነቱን ይወስዳል።

ወገኖች ያለው አክብሮት እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ከጅምሩ ግልጽ ማድረግ ይፈልጋል። ለነዚህ ጀግኖች ተገቢውን አክብሮትና ለከፈሉት መስዋዕትነት እውቅና ከመስጠት ወርዶ ራስን በዋጋ ቢስነትና ባዶነት ደረጃ ማውረድ ግን ለአገራችንም ሆነ ለህዝባችን የሚበጅ አይሆንም የሚል እምነት አለው። ከዛ ይልቅ ላገርና ህዝብ የሚጠቅመው የጀግኖቻችንን ፈለግ በመከተል እነሱ ሕይወታቸውንና አካላቸውን የሰጡለት እውነተኛ ዓላማ እታሰበለት ግብ እንዲደርስ የበኩልን አዎንታዊ አስተዋጽኦ ለማበርከት ቆርጦ መነሳት ይበልጥ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብሎ ያምናል። የዋጋ ቢስነትና ባዶነት ስሜት ተሸክሞ መንቀዋለሉ ክንዳቸውን የተንተራሱ ጀግኖች ሕይወትን አይመልስም። አካላቸው የጎደሉ ወገኖቻችንን አካልም አይጠግንም። በዚህ ፀሐፊ እምነት፣ ያንን የጀግኖች ሞትና የአካል መጉደል ተገቢ ክብር የሚያገኘው የባዶነትና የዋጋቢስነትን ስሜት አንግቦ ሥልጣን ለጨበጠ በማጎብደድ አይደለም። እነሱ መስዋእትነትን የከፈሉት ለዓላማ ስለሆነ፣ የነሱን መስዋእትነት መበቀል የሚቻለው ያን ዓላማ እግቡ ለማድረስ በልበ-ሙሉነትና በዓላማ ጽናት ለመቆም ሲቻል ብቻ ነው። ይህንን ግዳጅ ለመወጣት ደግሞ ሐቀኝነትንና ለዓላማው ያለህ ታማኝነትን ይጠይቃል።

ፕሮፌሰሮችና የጦር ጉዳተኛን በማወዳደር የቀረበው የሐጎስ ዮሐንስ ሓተታም ረጅም መንገድ የሚያስኬድ አይደለም። ሁሉም በሙያ መከበር ይኖርበታል። አገርንና ህዝብን ከጥቃት ለመከላከል የሠለጠነ ዘመናዊ ሠራዊት እንደሚያስፈልገን ሁሉ በግንባር ቀደምትነት ተሰልፎ በመዋደቅ ላይ የሚጎዳን ጀግና ለመታደግ የሚችል የሕክምና ባለሙያ ያስፈልጋል። አንድ አገር በወታደራዊ ጥበብ ብቻ ሊያድግ አይችልም። በመሆኑም በየሙያ ዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ያስፈልጋል። ይህ ፀሐፊ ከአንድ ተራ ወታደርና ከአንድ ፕሮፌሰር፣ የቴክኒክ ባለሙያ፣ የፋይናንስ ባለሙያ፣ ..ወዘተ መመረጥ የግድ ነው ቢባል ግን ባለሙያው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ላገሩ ወታደር ሆኖ ሊዋደቅም ስለሚችል ፕሮፌሰሮችን ለመምረጥ ይገደዳል። ፕሮፌሰሮቹን ለመምረጥ የሚያስገድደን ዋናው ምክንያት ግን አስፈላጊ ሲሆን እነሱም ላገራቸው ወታደር ለመሆን ስለሚችሉ ብቻ አይደለም። እነዚህ አገርን ለመከላከል የሚሰለፉ ወጣቶቻችንን ጨምሮ የአንድን አገር ህዝብ ቢቻል አንድም ሳይቀር ሁሉንም ፕሮፌሰሮች አድርጎ እንዲያመርትልን/እንዲያስተምርልን ከመመኘት ስለሚመነጭ ነው። ለአገርና ለህዝብ ሲል ሕይወቱንና አካሉን የሰጠ ወገንን ማክበርና የሚገባውን እንክብካቤ እንዲያገኝ ማድረግ ተገቢም ግዴታም ነው። ይሁን እንጂ አንድ የጦር ሜዳ ጀግና የፕሮፌሰሩን ሙያ ተክቶ ለመሥራት እንደማይችል ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል። የመምረጥ ግዴታ ከተጣለ የፕሮፌሰሩ ሙያ ይመረጣል ሲባል ለጦር ሜዳ ጀግናው የሚሰጠው ግምት ከማሳነስ እንዳልሆነ አንባቢ ልብ እንዲለው ይጠየቃል። ምርጫው ፕሮፌሰሩ ለዛ የጦር ሜዳ ጀግና አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ቁምነገሮችን የመፍጠርና የመመራመር ተልእኮን ሊወጣበት የሚያስችለው ለዓመታት ያካበተው እውቀትና ልምድ እንዳለው ግንዛቤ ማግኘት ይኖርበታል። ወደ ተጨባጭ እውነታ ስንገባም እያንዳንዱ ዜጋ ሙያውና ችሎታው እየተመዘነ በሚመጥነው ቦታ መቀመጥ ይኖርበታል። ሆኖም "አንድ ተራ የጦር ጉዳተኛ ኢትዮጵያዊ ጀግና ከአንድ በዓለም እውቅ ዩኒቨርሲቲ ከሚያስተምር ፕሮፌሰር የበለጠ የመገንዘብ፣ የማወቅና የመረዳት ችሎታ አለው" የሚለው አባባል ግን ሚዛኑን የሳተ አባባል ከመሆን ያለፈ ትርጉም አይኖረውም። ይህ ፀሐፊ፣ የሐጎስ ዮሐንስ ፕሮፌሰሮች ምን ዓይነት እንደሆኑ ለመገመት ባይችልም ባጠቃላይ ፕሮፌሰሮች ከአንድ ተራ ተዋጊ በላይ ሁኔታዎችን የመረዳት፣ የመገንዘብና የማወቅ ዓቅም እንዳላቸው ያለ ምንም መጠራጠር ያምናል። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ሐጎስ ዮሐንስ አለቃቸው አቶ መለስ ዜናዊ ባንድ ወቅት የሙሁርን ዋጋ ለማጣጣል ሲሞክሩ "ዋናው የሚፈለገው የኢህአዴግን ዓላማ ተቀብሎ ለመተግበር መቻል ነው፣ ይህንን ከቻለ ሥልጣን የሚጨብጠው ተራ መሃይምም ሊሆን ይችላል።" ሲሉ

3 የትርጉም ስሕተት ቢኖርበት ይህ ፀሐፊ ሐላፊነቱን ይወስዳል።

የሰነዘሩት አባባል እጅጉን እንደሚረካቸው ከጻጻፋቸው ለመረዳት ይቻላል። ለዚህም ይመስላል ሐጎስ ዮሐንስ እንደበቀቀን ከአለቃቸው የሰሙትን ሳያላምጡ የመድገም አባዜ ተጠናውቷቸው የሚስተዋለው። አንድ ተራ ወታደር አካሉ በጦር ሜዳ በመጉደሉ ብቻ በዓለም በታወቁ ዩኒቨርሲቲዎች ከሚያስተምር ፕሮፌሰሮች በላይ ኢትዮጵያን ሊያበለጽግ የሚችል ምርጥ ሰትራተጂን የመገንዘብ፣ የማወቅና የመረዳት አቅም ሊኖረው ይችላል ብለው ለማመን የገፋፋቸው እምነትም ከዚህ አጉል አምልኮ እንደሚመነጭ የሚያጠራጥር አይደለም። ለመሆኑ ሐጎስ ዮሐንስ ከዚህ ሥር እንደሚከተለው በማለት ያሰፈሩት፤ ተሳስተው ይሆን? ወይስ እንደተለመደው ተምታትቶባቸው? በእውቅ ዩኒቨርሲቲዎች ከሚያስተምረው ፕሮፌሰር በላይ በጦር ሜዳ አካሉ የጎደለ ተራ ወታደር "የበለጠ ኢትዮጵያን ለማበልጸግ አስተዋፅዖ ያለው ምርጥ ሰትራተጂን የመገንዘብ፣ የማወቅና የመረዳት አቅም እንዳለው እርግጠኛ ነኝ።" ብለው የሚያምኑ ስው የሚከተለውን እንዴት ሊያሰፍሩ ቻሉ ብሎ መጠየቅ አገባብ ይሆናል። የሚከተለውን ይመልከቱ፤

(ፓራግራፍ 5 ተመልከት)

> ***"ቤተሰቦቻቸውና ጓደኞቻቸው ተምረው የመጻእቱን ኢትዮጵያ ተስፋ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚረዱ ሰዎች አሉ። እነዚህም እንደ ጀግና ይቆጠራሉ"***

እውነቱን ለመናገር ሐጎስ ዮሐንስ ሰባት መስመር ከፍ ብለው ያስቀመጡትን የረሱት ይመስላል። "ተራ አገሩንና ወገኑን ለመታደግ አካሉ የጎደለ ዜጋ ስለ አገር ልማት ስትራተጂ በምርጥ የዓለም ዩኒቨርሲቲዎች ከሚያስተምሩ ፕሮፌሰሮች የበለጠ ግንዛቤ አለው" ብለውን ሲያበቁ፤ ከላይ ያሰፈሩትን ረስተውት ሳይሆን አይቀርም፤ ለመጻኢት ኢትዮጵያ ተስፋ እንዲሆኑ ቤተሰብና ጓደኛን የሚያስተምሩ እንደ ጀግና የምንቆጥራቸው ወገኖች አሉ ይሉናል። እዚህ ላይ ሐጎስ ለትምህርት ዋጋ እየሰጡ መሆኑን እንገነዘባለን። ትምህርት ዋጋ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ከሆነ ደግሞ ሐጎስ ዮሐንስ ከፍ ብለው ያብጠለጠሉዋቸው ፕሮፌሰሮች ለኢትዮጵያ መልካም እሴት ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚያጠራጥር አይደለም። ይህ ማለት ግን ፕሮፌሰር የሆነ ሁሉ እንከን የለሽ ነው ለማለት እንዳልሆነ አንባቢ ልብ ሊለው ይገባል። በቁጥር ሲሰላ ግምት ውስጥ የሚገቡ ባይሆኑም፤ ዓለማችን ውስጥ የገበዩትን እውቀት አስፈላጊ ላልሆነ ጉዳይ የሚያውሉ ፕሮፌሰሮች እንዳሉ የሚታወቅ ነው። ለዚህም ኢትዮጵያዊያን ፕሮፌሰሮች ብቻ ተለይተው የሚፈጽሙት አይደለም። ዋናው ቁም ነገሩ ግን ሐጎስ ዮሐንስ የተማረ የሰው ኃይል የመጻኢቱ ኢትዮጵያ ተስፋ እንደሆነ ማመናቸው ላይ ነው። ስለሆነም፤ ወጣቶቻችንን አስተምረው ለቁምነገር ለማብቃት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ወገኖቻችን ሊመሰገኑ ይገባል። እዚህ ላይ ሐጎስ የሐንስ የጠሉት ፕሮፌሰሮችን ሳይሆን ህወሓት/ኢህአዴግን የማይደግፉ ወይም ለዚህ ድርጅት የማያሸረግዱትን ይመስላል። ይህ ፀሐፊ ለሙያውና ለሙያው ብቻ ታማኝ የሆነን ሰው ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ያከብራል። ይህንን በሚመለከት ሪፖርተር ጋዜጣ እ.ኤ.አ ሐምሌ 24 ቀን 2011 በቆይታ አምዱ ላይ ቃለ-መጠይቅ ያደረገላቸው ዶክተር ኢዮብ ተስፋዬ *"ሪፖርተር፡- እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በተለይ ለዋጋ ግሽበቱ አስተዋጽኦ ያደረገው የብር መጠን መብዛት ሳይሆን፣ ከውጭ የገባው የዋጋ ግሽበት ነው የሚሉ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች አሉ? ምን አስተያየት አለዎት? ሲል ላቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ።*

***ዶ/ር ኢዮብ፡-*** በመጀመርያ ደረጃ እነዚህ ባለሙያዎች አይደሉም፡፡ የሰው ፊት እያዩ የሚኖሩና ከተሰቀሉበት ኮብራ መውረድ የሚያስፈራቸው ናቸው፡፡ ........" የሚል ነበር። ይህ ፀሐፊ አክብሮቱን የሚነፍጋቸው እነዚህ ዶ/ር ኢዮብ ከኮብራ ለመውረድ የሚፈሩ የሚሏቸው ዓይነቶችን

ነው። ስለሆነም ሐጎስ ዮሐንስም ፕሮፈሰሮችን ሳይሆን እነዚህ "ከኮብራ ለመውረድ የሚፈሩትን " መሆን ይኖርበታል። ከዚህ በተቀረ አንድ ፓራግራፍ ውስጥ ሁለት ተቃራኒ አቋሞችን ማንፀባረቅ የለማጅ ካድሬዎች የጀማሪ ስሕተት ነው ተብሎ ቢታለፍ ይሻላል። በዚህ ርእስ ዙርያ በጣም በሰፊው መጻፍ የሚቻል ቢሆንም ለአሁን እዚሁ ቢቋጭ በቂ ይሆናል።

(ፓራግራፍ 6 ተመልከት)

> ***"...... አእምሮየንና ህሊናየን የሚረብሹ በጣም ብዙ ጉዳዮች አሉ ። ይሁን እንጂ የጊዜ <u>እጥረትና የአቅም ማነስ ችግሮች ተዳምረው</u> ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ከኢሮብ ህዝቤ ያገኘሁዋቸውን ነጥቦች/መረጃዎች ላይ ትኵረት በማድረግ አስተያየቴን እንዳልሰነዝር ገድበውኛል።"***

ግሩም አባባል ነው! የጊዜው ነገር ከተነሳ ይህንን መረጃና መቋጫ አልባ ዝባዝንኬ ለመጻፍ የጠፋው ጊዜ እውነትም ሊያሳዝን በተገባ ነበር። ፅሑፉዎ የትኵረት አቅጣጫ የለውም። ፅሑፉዎ ለዓቅመ አዳም ያልደረሱ የኢሮብ ወጣቶችን ለጦርነት መመልመል ስብእናን የሚጻረር ወንጀል እንደሆነ በርእሱ ያስቀምጥና ስለ ምሥራቅ አፍሪቃ፤ ስለ ዳያስፖራ፤ በጦርነት አካላቸውን ስላጡና በዓለም የታወቁ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩ እውቅ ፕሮፈሰሮችን ማነጻጸር፤....... ወዘተ በመዘባረቅ ጊዜና ቦታን ፈጅቷል። እውነቱን ለመናገር የተነሱበት ነጥብ ላይ በማትኵር ለማስተላለፍ የፈለጉትን መልእክት ለማስተላለፍ ቢሞክሩ ኖሮ ያቀረቡት ሓሳብ በግማሽ ገጽ ቢበዛ ደግሞ በአንድ ገጽ ሊጠናቀቅ ይችል እንደነበር የሚያጠያይቅ አይደለም። እንዲህ ቢሆን ኖሮ ሐጎስ ዮሐንስ በከንቱ ያጠፉትን ጊዜ ለመቆጠብ በቻሉ ነበር። ሌላው (however, lack of time and capacity are limiting me….) በማለት ስለ አቅም ማነስ ያነሱት ነጥብ ልዩ ትኵረት የሚያስፈልገው ነው። እዚህ ራሳቸው ያመኑት ዓቅም ማነስ በፅሑፋቸው ውስጥ በስፋት ተንፀባርቆ የሚታይ ነው። በመሆኑም ሐጎስ ዮሐንስ አመኑት አላመኑት ፅሑፋቸውን ልብ ብሎ ለሚያነብ የዓቅም ማነስ ድክመቱ ጎልቶ የሚታይ በመሆኑ ብዙም የሚያከራክር አይደለም። ስለዚህ ለወደፊቱ ቢማሩበትና የዓቅም ማነስ ችግር እንዳለባቸው በመገንዘብ የመፃፍ አቅማቸውን ለማሳደግ ጥረት ቢያደርጉ መልካም ይሆናል። ለዚህም ብቃት ያለው የማያወላዳ መረጃ መሰብሰብ የመጀመርያ ተግባራቸው እንዲሆን ቢያደርጉ ይጠቅማቸዋል።

ሐጎስ ዮሐንስ በበጋ ወራት ወደ ኢትዮጵያ እየሄዱ እንደሚያሳልፉ ካወጉን በኋላ፤

(ፓራግራፍ 6 7ኛ መስመርን ተመልከት)

> ***"እ.ኤ.አ በ2007 ዓ.ም የበጋ ወራት ለዓቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆቻቸው ወደ ኤርትራ የሄዱባቸው ወላጆችን ተገናኝቼ ነበር። ቤተሰቦቼም የችግሩ ሰለባዎች ናቸው።"***

እዚህ ላይ ሐጎስ ዮሐንስ ለዓቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆቻቸው ወደ ኤርትራ የሄዱባቸው ቤተሰቦችን እንደተገናኙ ገልጿል። ልጆች ወደ ኤርትራ እየከበለሉ የሄዱባቸው ወላጆች መኖራቸው የማይታበል ሀቅ ነውና እንዲህ ዓይነት ችግር የገጠማቸው ቤተሰቦችን አግኝተው ሊሆኑ ይችላሉ። የራሳቸው ቤተ-ሰብም የተጠቀሰው ችግር ሰለባ እንደሆኑ ይገልጻሉ። የችግሩ ሰለባ የሆኑ ቤተ-ሰቦች መኖራቸው እውነት ነውና የሐጎስ ቤተሰቦችም የችግሩ ሰለባ ሆነው ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል። ችግር የሚሆነው እነዚህን ወጣቶች ወደ ሻዓቢያ የሚያሰኮበልለው የኢሮብ መብት ተሟጋች ማኅበር (ኢ.መ.ተ.ማ) ነው ብሎ ለመናገር የሚያስችል ማስረጃም ሆነ መረጃ ለማቅረብ መቻሉ ላይ ነው።

ወደ ሻዓቢያዋ ኤርትራ የኮበለሉ ልጆችን በሚመለከት የተሟላም ባይሆን ይህ ፀሐፊም የተወሰነ መረጃ ለማሰባሰብ ሞክሯል። ያገኛቸው መረጃዎች ግን የሚያሳዩት ሐጎስ ዮሐንስ የሚቀባጥሩትን የሚጻረር ሆኖ ይገኛል። ስለዚህ፤ ልጆቻቸው ወደ ሻዓቢያዋ ኤርትራ የኮበለሉባቸው ቤተሰቦችን ተገናኝቶ ስለሁኔታው በማወያየት ተጨባጭ ማስረጃና መረጃ ከነማጣቀሻው አቅርቦ ወንጀለኞችን ለመፋረድ መነሳትና ልጆቻቸው የኮበለሉባቸው ቤተሰቦች ተገናኝቶ ማውራት እጅጉን የተለያዩ ነገሮች ናቸው። በመሆኑም፤ ሐጎስ ዮሐንስ የባጥ የቆጡን በማውራት መቀባጠርና ተጨባጭ ነገር ይዞ አደባባይ መውጣት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸው ሊያቁ ይገባል። ሐጎስ ዮሐንስ ልጆቻቸው ወደ ሻዓቢያዋ ኤርትራ የኮበለሉባቸው ቤተ-ሰቦችን አግኝተው ማነጋገርን እንደ ማስረጃ ቆጥረውታል። ይህ ማስረጃቸው ግን ጠለቅ ብሎ ሲዳሰስ ለመረጃም አይበቃም። ይህንን "ግኝታቸው" ወደ ፍርድ ቤት የሚያቀርቡት ቢሆን ኖሮ እንደ ጭብጥ ሊያዝላቸው የሚችለው እንደተለመደው በህወሓት/ኢህአዴግ ፍርድ ቤት ብቻ መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል። ገለልተኛ ፍርድቤት ጋር ይህንን እንደ ጭብጥ ይዘው ቢቀርቡ መሳቂያ ሊሆኑ እንደሚችሉና ከዛም አልፎ መልካም ስም በማጉደፍ ሊያስከስሳቸው እንደሚችል ሊገነዘቡት ይገባል። ስለዚህ ሐጎስ ዮሐንስ እውነት ባልሆነ ነገር ያወናበዱትን ወገንና በበሬ ወለደ መልካም ስማቸው ያጠፏቸውን ዜጎች ይቅርታ ቢጠይቁ መልካም ይሆናል።

በክፍል ስድስት እስከምንገናኝ በሰላም እንቆይ!!!

ይቀጥላል...............

ሐምሌ 20 ቀን 2011 ዓ.ም.ፈ.

አስተያየት ለመስጠት balibizema@yahoo.com መጠቀም ይቻላል።